# ፓሪ ሞድ ለብሳለች . . . . . . .

ከበልጅግ አሊ

-፩-

ምንድነው ቁንጅና ፣ ምንድነው ውበት፣
ፀባይ ከሌለበት ፣ ቢሽቀረቀሩት ፣
ጊዜው ይገፋና ፣ ውበቱ ሲረግፍ ፤
የተደባበቀው ፣ በውበት ብዛት
ፍጥጥ ብሎ ይወጣል ፣ ዐመል ወደፊት ።

በ. አሊ

ወቅቱ የንጉሡ ዘመን ማክተሚያ አካባቢ ሲሆን አዲስ አበባ ውስጥ እገሌ እገሌን ገደለው፣ እገሌ ሕይወቱን አጠፋ ፣ ተሰቀለ ፣ ተገደለ ፣በጩቤ ተወጋ የሚሉ ተባራሪ ወሬዎች የሕዝቡን ሰላማዊ ኑሮ በተደጋጋሚ ያደፈርሱት ነበር።በከተማው ውስጥ የሚፈፀመውና የሚወራው ወሬ ሁሉ የሚያስፈራ ነበር ።

- ተክለ ሐይማኖት መንግሥት ሰው ሰቅሏል አሉ!
- ምን አድርጎ ? ሌላው ይጠይቃል።
- እህቱን ደፍሮበት አልጠቀልል ቢለው ደፋው።
- የት አባቱ እንኳን !
- ገዳይ ከመሰቀሉ በፊት ፎክሮ ነው አሉ የተሰቀለው ።
- ምን አለ ?
- ይህን ሴት አውል ከገደልኩ ብሞትም አይቆጨኝ አለ ።
- ደግ ብሏል ።
- የሟች ቤተሰቦች እልል አሉ።
- ምን ያደርጋል እልልታ ልጃቸውን አይመልስላቸው ።

ሌላ ጊዜ ደግሞ

- አብነት ቡና ቤት ጋር ሰው ተሰቅሏል ይባላል።
- ምን አድርጎ ?
- ሰው ገሎ ነዋ።
- ምን አድርጎት ገደለው?
- ሚስቱን ቢያይበት ድሮም ይጠረጥረው ነበርና አሳቻ ቦታ ጠብቆ ደፋው!
- ላልጠፋ ሴት ?
- ምን ማለትህ ነው? ሚስቱ አደለች እንዴ ?

ሌላ ሠፈር ደግሞ

- እገሌ እገሌን ገድሎ ጥይቱን ጠጥቶ ሞተ ።
- በምን ምክንያት ?
- በመሬት ክርክር ምክንያት ።
- የሟች ቤተሰቦች ሬሳው ይሰቀልልን ብለው ንጉሡን ጠይቀው እንቢ ተባሉ አሉ ።
- ምን ማለታቸው ነው የሰው ልጅ ቋንጣ ነው እንዴ ?

- እገሌ እራሱን ሰቀለ ።
- ለምን ልጄ?
- ቢያጣ ቢቸግረው ከመለመን ከመዋረድ ብሎ እራሱን አጠፋ ።

እነዚህ ሁሉ በየቀኑ አዲስ አበባ ውስጥ የሚፈፀሙ ክስቶችች ነበሩ ። የልደታ ሠፈር ተራም ደረሰና  አንድ ቀን ይህ የሽብር ወሬ አካባቢውን አናጋው ። በምሽት የጥይት ጩኸት ያን ኤሌትሪክ ለመቆጠብ ቀድሞ የተኛውን ሕዝብ  ፀጥታውን አደፈረሰው ። ነዋሪው ከቤት ወጥቶ ወደ ተተኮሰበት ቦታ ይበር ጀመር ። ቀድሞ የደረሰው አርፍዶ ለመጣው ወሬውን አቀበለው።

- ኪዳኔ ቆንጅትን ገደላት !!!
- እንዴት?
- በሽጉጥ ገድሏት እራሱን አጠፋ ።
- አይ ደጉ ሰው! ሰው መካሪ አልነበረም እንዴ፣ ምን ሠይጣን አገኘው?
- ምን ያድርጋት ታዲያ ታኮ ጫማዋንና ፓሪሞድዋን አድርጋ ፣ ፀጉሯን ተተኩሳ መበራገድ ሆነ ። ትዕግሥትም ያልቃል እኮ !
- ቢሆንስ አያስመክራትም ነበር ?
- ምን ያድርግ ? በሱም አይፈረድ ከወንድ ጋር ነው ተኝታ ነው የተገኘችው አሉ እኮ !
- ታዲያ እሱንስ ገደለው ?
- ምን ይገድለዋል አመለጠ እንጂ ።

ሴቶቹ ደግሞ ራቅ ብለው ።

- ምስኪኗን እኮ ገደላት።
- መሐኗን ልጅ እንኳ ሳትወልድ ።
- ጭኗንና ብልቷን ነው የመታት ። ሆዷንም አግኝቷታል አሉ ።ብትተርፍ እንኳን ሌላ እንዳታገባ ነው ያበላሻት።
- አይ ምስኪን ። ያ ሁሉ ቁንጅና አፈር ሊበላው ።
- እሷም እኮ አብዝታው ነበር ።ጎረቤቶቹ የሚያወሩት ሌላ ነው።
- ባካችሁ ተውኝ ! ቆንጆ ሰው ፈላጊው ሰለሚበዛ ይስራውም አይስራውም በብልግና ይጠረጠራል።መታማቱ እንደሁ አይቀር ።ሰው ከሰው ላይ አይወርድም ። ጥሩ ትዳር ሰላላቸው ቅናት ነው ።
- ወሬውን ስትሰማ ሁሉን እርግፍ አድርጋ ቤት አትቀመጥም ነበር ?
- ለማን ብላ ነው ቤት ውስጥ ተዘግታ የምትቀመጠው?
- ከመሞት  ይሻላታል ብዬ ነዋ !
- እርሶ ደግሞ አርፈው ይቀመጡ። አሁን የእኛ ኑሮ ከሞት ተሽሎ ነው ?እቤት ተዘግተን እየዋልን ፣ ማታ ማታ ከጠጅ ቤት መልስ እየተቀጠቀጥን፡፡ ከቴም ኑሮ።

ሁሉም በነጠላቸው ጫፍ ዓይናቸውን አበስ እያደረጉ ያለቅሳሉ ።ለሟችም ፣ ለራሳቸውም ኑሮ ።

የቆንጅትና የኪዳኔ ታሪክ ልደታ ውስጥ ለብዙ ዘመናት ይታወስ ነበር። ጊዜው ረዝሞ ምንአልባት  ዛሬ እዛ ሠፈር ውስጥ የሚያስታውሰው ባይገኝም፣ በወቅቱ ጉድ ተብሎ የታለፈበት ፣እሷን ያያችሁ ተቀጡ ! ተብሎ የተስፈራራበት ነበር ። ታሪኩ የልደታ “ሮሚዮና ዡሌት“ ታሪክ ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ቆንጂት ልደታ ውስጥ ሥልጣኔን አስገቡ ተብለው ከሚመደቡት ዘመናዊ ሴቶች ውስጥ ነበረች። ዘናጭ ልብስ ፣ ነጠላ ሳይደርቡ መውጣት ፣ ታኮ ጫማና፣ ፓሪ ሞድ ማድረግ፣ ፀጉር መተኮስ፣ በአጠቃላይ በወቅቱ ዘናጭና ፣ዘመናዊ ሰው የሚያስብሉ አለበበሶችን ታዘወትር ነበር ።  ቆንጂት ከአለባበሷ በተጨማሪ ውብ ከመሆኗ የተነሳ የማይመኛት የለም ።

ፓሪሞድ ላብሳለች ፣
ሹራብ ደርባለች ፣
ጸጉሯን ተተኩሳ ፣
ሰዓት አድርጋለች ። ተብሎ በወቅቱ የተዘፈነው ለእንደእሷ ዓይነቶቹ ነው ።

የቆንጅት ባል ኪዳኔ ደግሞ በሰፈር ውስጥ የተከበረና የተወደደ ፣ ዝምተኛ ፣ ሰላምተኛ ፣ ታታሪ ፣ ኀበዝ ፣ ሚስቱን የሚያምንና የሚወድ፣ የሚያከበር፣በጎረቤቶቹ የተከበረ፣መካሪ፣ሰው አስታራቂ ነበር ።

ቆንጅት ቆንጆ በመሆኗ በሰፈር ውስጥ ደግሞ ያልተለመደውን መሽቀርቀር በማብዛቷ ምክንያት ወሬዎች ይነፍሱ ጀመር ። የትም ትሂድ የትም ሁል ጊዜ የምትጠረጠረው በዝሙት ብቻ ነው ። በየመንገዱም የወንዱ ዐይን ከእሷ ላይ አይነሳም ።እየዋለ እያደር ባል ይህንን ሁኔታ ሊቀበለው አልቻለም ። ጭቅጭቅ ትዳራቸው ውስጥ ገባ ። ታዲያ አንድ ምሽት ሲፈራ የነበረው ደረሰ ።

ኪዳኔ በቅናት ያራል ። ቆንጅት ግን የባሏን ምን ያህል መብገን ሳታመዛዝን ቀርታ ዝነጣዋን በሰፊው ተያይዛዋለች።ባል ይወስናል ።ንዴቱና ቅናቱ ወደ በቀል ይለወጣል። ይህንን ጉዳይ ከመጨረሻው ለማድረስ ያስባል።ሚስቱ ከውጭ መጥታ ልብሷን ስትቀይር ሽጉጡን አቀባብሎ ገብቶ በተደጋጋሚ ብልቷ ላይ ተኩሶ ካቆሰላት በኋላ የሞተች መስሎት ሽጉጡን ጠጥቶ ይሞታል ።

“እንደወደድኩሽ ፤ ገደልኩሽ
እንደገደልኩሽ ፤ ሞትኩልሽ“

ኦቴሎ

ቆንጅት አልሞተችም በህክምና ብዛት ዳነች ። ግን አካለ ጎደሎ ሆና ታነክስ ጀመር። ጊዜ ሲያልፍ ሁሉም የተወራው ውሸት እንደሆነ ተረጋገጠ።ከወንድ ጋር ተኘታ እንዳልነበረም ታወቀ። እንዲያውም ቆንጅት ለቅሶ ቤት ለቀስተኛውን ራት አብልታ መመለሷ ነበር ። ቆንጅትን የሠፈሩ ሰው በደንብ አወቃት። ምንም እንኳ ቁንጅናዋ በማንከሷ ምክንያት ቢቀንስም፣ ሌላ ወንድ የማግባቱ ጉዳይ ቢያከትምም ፣ የተረፈውን ሕይወቷን ግን እንደተከበረች ልደታ ውስጥ ኖረች።

ይህንን ሁሉ ጉድ እንደ ኢያጎ ሆኖ ያቀነባበረው የሚች ልጅ ፣ የቆንጅት የእንጀራ ልጅ ንጉሤ የሚባል ነበር ። ንጉሤ ከሕፃንነቱ በተንኮል ያደገ የሠይጣን ቁራጭ ነበር ።ቆንጅት የልደታ ዴዝዴሞና ፣ ንጉሤም ኢያጎ ፣ ሚችም ኦቴሎ ሆነው ለዘላለም በልደታ ውስጥ ይታሰባሉ ።

ሚችና ቆንጅት ተጎዱ። ንጉሴ ግን በዚህ ሰይጣናዊ ስራው ምን ያህል እንደተደሰተ መገመት ባይቻልም የአባቱን ሞት ግን የጠበቀ አይመስለኝም ። አባቱ ከሞተ በኋላ የገንዘብ ችግር ገጥሞት ነበር ። ለብዙ ጊዜ ከተቸገረ በኋላ ደርግ ሲመጣ አብዮት ጥበቃና የመኢሶን ካድሬ ሆነ። እንደገና የደም ጥማቱን ለማርካት ይሯሯጥ ጀመር ። በቀይ ሽብር የብዙ ወጣቶችን ደም አፈሰሰ።

ይህ ነበር የልደታ “የሮሚዮና ዡሊየት“ ታሪክ።

በሃገራችን በሴቶች ላይ የሚፈፀመው ግፍ ብዙ ነው ። በባል መደብደብ ፣ በቤተሰብ ውስጥ መጨቆን የተለመደ ነው ። ሴቶች ገና ሕጻናት እያሉ ነው ይህንን የሰቆቃ ኑሮ የሚጀምሩት ። ቤተሰብ ባለግሽ አልባለግሽ ብሎ ሲቀጠቅጣቸው ይገኛል ።ባል ፣ እጮኛ ፣ ፍቅረኛ ወይም ገና የተመኘ ሁሉ ለምን እንቢ ተባልኩ ብሎ በቅናት ደብኖ ሕይወት እስከማጥፋት ወይም በአካል ላይ ከባድ ጉዳት እስከማድረስ ይደርሳል ።

አሁን የሃገረችን ሴቶች ሙሉ በሙሉ ሃገራቸውም ላይ ባይሆን በሰለጠነው ዓለም ላይ በቁንጅና ምክንያት የሚደርስ ችግር እንዳለ ሁሉ ደግሞ በቁንጅና ምክንያት ለሃገር

መስራት፣ ሃገርን ማስጠራት እንደሚቻል በቅርብ ቀን ጀርመን ውስጥ የተፈፀሙት ሁለት ድርጊቶች ያረጋግጣሉ ።የሣራ ኑሩና የምህረት ክፍሌ ዜና የጀርመንን ጋዜጦች ሲዘግቡት ከርመዋል ።

ጥቁር በጣም በማይከበርበት ጀርመን ሀገር ውስጥ ይህ ይሆናል ብሎ ማሰብ ይከብዳል ። ግን የተለመደውን የጀርመኖች ዘረኝነትን እንኳ ሳይቀር የኢትዮጵያውያኑ ቁንጅና ሊከድ አልቻለም።



ሳራ ኑሩ

በመጀመሪያ ሁሉም የደነቀው የጀርመንን ሞዴልነት(Top Model) ያሸነፈችው ሳራ ኑሩ የምትባል ውብ ኢትዮጵያዊት ነች ። ይህችን ልጅ በዚህ ሃገር የሚኖሩ ኢትዮጵያኖች ይህንን ውድድር እንድታሸንፍ ጠዋት ማታ ፀልየውላታል። ሳራ ዓይን አፋርነት ያላት ፣በኢትዮጵያዊነቷ የምትኮራ ለመሆኗ ከሰጠቻቸው ቃለ መጠይቆች መረዳት ይቻላል ።



ሳራ ኑሩና ካርል

በዚች ውብ ልጅ ያልተደነቀ ፣ በቁንጅናዋ ያለተማረከ ፣ በፈገግታዋ ያልረካ ፣ በጨዋነቷ ያልተገረመ የጀርመን ሰው ይኖራል ለማለት ያዳግታል ። ያው የለየላቸው የናዚ ተከታዮች ካልሆኑ በስተቀር ሌሎቹ ጀርመኖች ተደሰተዋል ።ሳራ ኑር ተዋቂ በመሆኑዋ ምክንያት ሃገሯን ለማስታወስ ቃል ገብታለች ። ካርል ሃይንዝ ቦም ከሚባለው የታወቀው የፊልም አክተር የነበረና ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ ውስጥ ሕዝብ ለሕዝብ (*Menschen für Menschen*) የሚል ድርጅት አቋቁሞ ከዘመነ ደርግ እስከ አሁን ታላቅ እርዳታ ከሚያደርገው ሰው ጋር አብራ እንደምትሰራ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥታለች ።



ሰለ ካርል ሃይነዝና እሱ ለኢትዮጵያ ያደረገውን ለመፃፍ ከተነሳሁበት ርዕስ ውጭ ቢሆንም አንባቢያን ግንዛቤ እንዲኖራችሁ ያህል ትንሽ ልጥቀስ።ካርል ሃይንዝ(Karlheinz Böhm)በአውስትርያና በጀርመን የተከበረ የነበረ የፊልም አርቲስት ካርል ሃይንዝ ታወቀ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ላይ ውድድር አቀረበ።ይኸውም ይህንን ፕሮግራም ከሚከታተሉት ተመልካቾች ውስጥ አንድ ሶስተኛው ተመልካች አንድ የጀርመን ማርክ ወይም ሰባት የኦስትሪያ ሽልንግ ወይም አንድ የሲውዘርላንድ ፍራንክ ከሰጠ ወደ ኢትዮጵያ ሄጄ እረዳለሁ በማለት 1981 እ.አ.አ. ቃል ገባ ። የተባለው ገንዘብ አልተሰበሰበም ። ውድድሩን ግን አሸነፈ።በወቅቱ የተገኘውን ገንዘብ ይዞ ወደ ኢትዮጵያ ሄዶ ርዳታውን ጀመረ ። ከዛ ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ እየኖረ እርዳታ መስጠቱን ቀጠለ። አውሮፓ ያለውን ድሎት ጥሎ በደስታ የተቸገረን ሕዝብ እየረዳ ኢትዮጵያዊቷን ወይዘሮ አልማዝን አግብቶ ይኖር ጀመር። የጀርመን፣የኦስትሪያና የሲዊስ ሕዝብ ይህንን አርቲስት ሰለሚያምን ብቻ ብዙ እርዳታ አድርጎለታል ።

ሳራ ኑር ከዚህ ሰው ጋራ ለመስራት ማሰቧ ፣ ሃገሯን አለመርሳቷ ፣ ለድሃና ለተቸገረ መቆሟ የሚያመለክተው ቁንጅናና ጠባይ መታደሏን ነው ።ሳራና ካርል ሃይንዝ አንድ ላይ በመሆን ብዙ ሥራዎች ለመሥራት እየተዘጋጁ እንደሆነ ተነግሯል ።




ቡርኖ ሹበርታና ምህረት

ሌላዋ ቆንጆ ሞዴል ደግሞ ሰሞኑን የጀርመንን ጋዜጦች ያጥለቀለቀችው ምህረት ክፍሌ ነች። ምህረት የሃያ ሰባት አመት ወጣት ነች ። ምህረት ከፍሌ በቁንጅና ተወዳድራ አይደለም የታወቀችው ። ይህንን አጠገቧ

የምታዩት ግለሰብ የ89 አመቱ ቢራ በመጥመቅና በመሸጥ ቢሊዮኔር የሆነ ግለሰብ አግብታ ነው ።

ይህ ሃብታም ቡርኖ ሹበርት ይባላል ። ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ በአውሮፓ የታወቀውን የቢራ ፋብሪካ ሄንነር ቢራ (Henninger) በማውጣት ሃብታም የሆነ ነው ። ይህ ግለሰብ 1979 እ.አ.አ . የቢራ ፋብሪካውን ሽጦ ለእንስሳት ተከራካሪ የሆነ ድርጅት አቀቁሞ ይገኛል ።



የጋብቻቸው ቀን

የሁለቱ ፍቅር የተጀመረው ምህረት በአስተናጋጅነት ተቀጥራ በምትሠራበት ሆቴል ውስጥ ነው ። ቡርኖ ገና እንደየኋት ነው የወደድኳት ነው የሚለው ። እሷ ደግሞ ቡርኖ ለኔ እንደተቀደሰ ሰው ነው የማየው ትላለች ። ይህንን ሁሉ ወጣ ገብ ሁኔታ አልፋ የምትወደውን ሰው በማግባቷ በበኩሌ ደስተኛ ነኝ ። ምህረት የሠርጓ ቀን በሃገራችንን ልብስ አልወጣችም ። የጀርመን የባህል ልብስ አድርጋ ነው የተሞሸረችው:ይህንን በማድረጓ ጥፋተኛ ነች ለማለት አደለም ።

ጀርመንም ቢሆን ሁለተኛ ሀገሯ ነው ።ግን ምህረትም እንደ ሳራ ሃገራችንን የሚጠቅም ነገር ለማድረግ ብትነሳሳ አብሯት የሚከተል ስም ይዛ ትጓዛለች ። በሕዝብም ዘንድ በቁንጅናዋ ብቻ ሳይሆን በበጎ ሥራ የተወደደች ትሆናለች ብዬ አምናለሁ ።

ካርል ሃይንዝ አንዴ በጀርመን ቴሌቪዥን በሰጠው መግለጫ “የኢትዮጵያ ዋናው ችግር ሴቶች በሕብረተሰቡ ውስጥ የሚደረግባቸው ጭቆና ነው ። ይህ ደግሞ ሀገሪቷን ለድህነት ዳርጓታል“ ብሎ ተናግሯል ። የሃገራችን ሴቶች በሃገራችን ጉዳይ ላይ ሙሉ በሙሉ ካልተሳተፉ ሃገራችን በግማሽ ወገኗ ማለትም በወንድ ብቻ ከድህነት እናላቅቃታለን ማለት ከቀልድ አያልፍም ።

በውጭ ሃገር በልዩ ልዩ መንገድ ከፍተኛ ቦታ የደረሱ ኢትዮጵያውያን አካባቢያቸውን በመመሰል ሃገራቸውን ረስተው በፈረንጅ ችግር ላይ ሲባዝኑና ፣ ሲማስኑ ይገኛሉ ። እነዚህ የሚናገርለት ላላጣው የፈረንጅ ችግር የሚያሽቃብጡ ሁሉ ወደ ትውልድ ሃገራቸው ችግር ፊታቸውን ቢመልሱ በዛች ሃገር ድህነትም በቅርብ ሊጠፋ ይችላል ባልልም አስተዋፅዖቸው የማይናቅ ለውጥ ያመጣል ብዬ አምናለሁ ።

ሰለ ሃገራቸን የሚያስብ ሁሉ በሰላም ይክረም ።

በልጅግ አሊ